17ኛ ዓመት ቁጥር 7
17th Year No. 7

ባህር ዳር ሰኔ 20 ቀን 2004 ዓ/ም
Bahir Dar June 27th , 2012

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት
# ዝክረ ሕግ
# ZIKRE HIG
## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

| በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State | ✉ 1324<br>ያንዱ ዋጋ ብር 6.80<br>Unit price 6.80 |
|---|---|---|

**ማውጫ** | **Content**

**አዋጅ ቁጥር 195/2004 ዓ.ም**
**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት የብድር ዋስትና ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ**

**Proclamation No. 195/2012**
**The Amhara National Regional State Micro and small Enterprises Development Credit Guarantee Fund Establishment Proclamation**

## አዋጅ ቁጥር 195/2004 ዓ.ም

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት የብድር ዋስትና ፈንድን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ**

ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በክልሉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ፤

የሥራ አጥነትና ድህነት ችግርን ለማቃለል እና የኢንዱስትሪ ልማት ለማፋጠን ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ያላቸው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ፤

## Proclamation No. 195/2012

**A proclamation Issued to provide for the Establishment of Micro and Small Enterprises Development Credit Gvarantee Fund in the Amahara National Regional State**

WHEREAS, the role that micro and small enterprises have is high for the Region’s social and Economical development;

WHEREAS, it has been found that the role of micro and small enterprises is high to mitigate the problem of joblessness and proverty and to speed up industrial development thereof;

ነባር ኢንተርፕራይዞችን ለማጠናከርና አዳዲስ ኢንተርፕራይዞችን ለመፍጠር ያለባቸውን የገንዘብ እጥረት ችግር ማስወገድ አስፈላጊ በመሆኑ ፤

አበዳሪ ተቋማት ብድር ለመስጠት ያለባቸውን ስጋት ለማስወገድና በነፃ ገበያ መርህ በውድድር ጥራትና ብቃት ያለው የብድር አቅርቦት እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የኢፌዴሪ መንግስት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጅና የድጋፍ ማዕቀፍ በክልል መንግስት የብድር ዋስትና ፈንድ መቋቋም እንደሚችል የሚፈቅድ በመሆኑ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለዉ የብሔራዊ ክልሉ ህገመንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1 ድንጋጌ ሥር በተሰጠዉ ሥልጣን መሰረት ይህንን አዋጅ አዉጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት የብድር ዋስትና ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 195/ 2004 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ዉስጥ:-

1) “ኤጀንሲ ” ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ማለት ነዉ::

2) “ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ» ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤትና የቤተሰብ አባላትን □ ምሮ □ስከ 5 ሰዎች ቀጥሮ የሚያሠራ ወይም/ እና የጠቅላላ ካፒታላቸው /Total capital/ መጠን በዋጋ ሕንጻን ሳይጨምር:-



WHEREAS, it has become necessary to get rid of shortage of money of enterprises so that the existed ones will be strengthen and new of same be created thereby;

WHEREAS, it has become necessary to eradicate threats of credit institutions to provide loan, and make available quality and efficient credit delivery on the principle of free market competition;

WHEREAS, the micro and small enterprises development strategy and support framework of the Government of FDRE, allow to establish credit guarantee fund by regional state thereof;

NOW, THEREFORE, the Amhara National Regional Copuncil, in accordance with the power vested in it under Article 49 sub – article 3/1 of the Revised Constitution of the National Region, hereby proclaims this proclamation.

## PART ONE

## GENERAL

### 1. Short Title

This proclamation may be cited as “the amhara National Tegional State Micro andsmall enterprises Development Credit Guarantee Fund Establishment Proclamation No 195/2012.”

### 2. Definition

In this proclamation, unless the context requires otherwise:

1. “Agency” means the Amhara National Regional State Micro and Small Enterprises Development Agency.
2. “Microenterprise’’ means including the owner of interprise and memners of the family that shall recruit and cause to work until five persons or/and the total capital amount not including the building:

ሀ. በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,000 (ሀምሳ ሺ) □ልበለ□ ፣

ለ. በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ) ያልበለጠ ኢንተርፕራይዝ ነው::

3) "አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ» ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤትና የቤተሰብ አባላትን ጨምሮ ከ6 □ስከ 30 ሰዎች ቀጥሮ የሚያሠራ ወይም/ እና የጠቅላላ ካፒታላቸው/Total capital/ መጠን በዋጋ ሕንጻን ሳ□□ ምር፤

ሀ. በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,001 (አምሳ ሺ. አንድ) □ስከ 500,000(አምስት መቶ ሺ) □ልበለ□ ፣

ለ. በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከብር 100,001 (አንድ መቶ ሺ. አንድ) □ስከ 1,500,000 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ) ያልበለጠ ኢንተርፕራይዝ ነው::

4) "የብድር ዋስትና ፈንድ /credit guarantee fund/" ማለት ከአበዳሪ ጋር በሚደረግ ስምምነት መሰረት ተበዳሪ ስምምነት በተደረሰባቸው ምክንያቶች ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት አጋጥሞት ብድር መመለስ ሲሳነው ለአበዳሪ ሊከፈል የሚችል ገንዘብ ነው፡፡

5) "ቦርድ" ማለት የብድር ዋስትና ፈንዱን በበላይነት ለመምራትና ለመቆጣጠር በዚህ አዋጅ የተቋቋመ የፈንዱ አስተዳደር የበላይ አካል ነው::

## 3. ዓላማ

በዚህ አዋጅ መሰረት የተቋቋመው የብድር ዋስትና ፈንድ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ያለባቸውን የገንዘብ (የካፒታል) እጥረት ለማስወገድና አበዳሪዎች ያለስጋት በበጎ ውድድር ስፋትና ጥራት ያለው ብድር እንዲያቀርቡ ለማድረግ የሚያስችለዉን ሁኔታ መፍጠር ነዉ፡፡

a. Not more than 50,000 (fifty thousand) Birr in the service sector,

b. Enterprise is not more than 100,000 (one hundred thousand) Birr in the industry sector.

3. "small enterprise" means including the owner of enterprise and members of the family that shall recruit and cause to work six upto 30 persons or/ and the total capital amount not including the building :

a. Not more than from 50,001 (fifty thousand Birr) to 500,000/ five hundred thousand Birr/ in the service sector,

b. Enterprise is not more than from 100,001 (one hundred one thousand Birr) to 1,500,000 (one million and five hundred thousand Birr) in the industry sector.

4. "Credit guarantees Fund" means the money that may be payed when the debtor could not pay the loan as per the agreement made with the Creditor due to *force majure*.

5. "Board" means a body established in accordance with this proclamation to adminster and supervises the fund thereof.

## 3. Objective

The objective of the credit guarantee fund, established pursuant to this proclamation, is to creat condusive condition which enables to provide huge and quality loan on sound competition; and to avoid the shortage of money/ capital/ that Micro and Small Enterprises encountered thereon.

## 4. ስለ ብድር ዋስትና ፈንድ መቋቋም

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ልማት ለመደገፍና ያለባቸውን የብድር አቅርቦት ችግር ለማስወገድ ከዚህ በኋላ "የብድር ዋስትና ፈንድ" እየተባለ የሚጠራ ፈንድ በዚህ አዋጅ መሰረት ተቋቁሟል፡፡

## 5. የብድር ዋስትና ፈንዱ መጠን እና ምንጭ

1. የብድር ዋስትና ፈንዱ መጠን በክልሉ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ በብደር ዋስትና ፈንድ ተጠቃሚ ለሚሆኑ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በየአመቱ ሊሰጥ የታቀደው የብድር ዕቅድ ሃያ በመቶ/20%/ ይሆናል፡፡
2. የብድር ዋስትና ፈንዱ ምንጭ፣
   ሀ. የክልሉ መንግስት በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚመድበው በጀት፣

   ለ. የብድር ዋስትና ፈንድ ተጠቃሚ የሚሆኑ ኢንተርፕራይዞች የሚከፍሉት 1% የአገልግሎት ክፍያ፣

   ሐ. ከሌሎች የሀብት ምንጮች ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት የተሰበሰበው ገንዘብ በኤጀንሲው ስም በሚከፈት ሂሳብ በአበዳሪ አነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት የሚቀመጥ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## ስለ ብድር ዋስትና ፈንዱ አስተዳደር አካላት

## 6. ስለ ፈንዱ አስተዳደር

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ብድር ዋስትና ፈንድ አስተዳደር የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡

## 4. Establishment of Credit Guarantee Fund

The fund/ hereafter called" credit guarantee fund" /is established by this proclamation to support the Development of Micro and Small Enterprises and thereby avoid problem of loan delivery they have.

## 5. Amount and source of Credit guarantee Fund

1. The amount of credit guarantee fund shall be 20% of the planned credit to be given annually to the micro and small enterprises, beneficiaries of the credit guarantee fund, by the micro and small enterprises development agency of the region.
2. The source of the credit guarantee fund shall be:
   a. The budget whuch shall be allocated by the Regional Gevernment pursuant tosub-article 1 of this Article;
   b. 1% of service charge to be paid by the enterprises that are the beneficiaries of the credit guarantee fund;
   c. From other sources.
3. The money collected pursuant to sub –article 2 of this Article, shall be put by the creditor of small credit and saving institutions in the account opened in the name of the agency.

# PART TWO

## Credit Guarantee Fund Administration Bodies

## 6. Fund Administration

The administration of micro and small enterprises development fund shall have the following bodies:

1. ከዚህ በኋላ "ቦርዱ" እየተባለ የሚጠራ የብድር ዋስትና ፈንድ አስተዳደር ቦርድ፤
2. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ፡፡

## 7. የብድር ዋስትና ፈንድ ቦርዱ አባላት

የብድር ዋስትና ፈንድ ቦርድ አባላት ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማትና ከብድር ዋስትና ፈንድ አስተዳደር አኳያ በዋናነት የሚመለከታቸው አካላት ሲሆኑ ቁጥራቸውም ከአምስት እስከ ሰባት ሆኖ በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሰየሙ ይሆናል፡፡

## 8. የቦርዱ ተግባርና ኃላፊነት

ቦርዱ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

1. የብድር ዋስትና ፈንዱን በሚመለከት ሪፖርቶችን ያዳምጣል፣ መመሪያዎችን ያወጣል፣
2. በአባዳሪ ድርጅቶችና በጥቃቅን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ መካከል አለመግባባት ሲከሰት መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤
3. የብድር ዋስትና ምንጮችን በማፈላለግ የዋስትና ፈንዱን ያጠናክራል፤
4. የቦርዱን የስብሰባ ጊዜና ቦታ እንዲሁም የውስጥ አሰራር በሚመለከት የራሱን መመሪያ ያወጣል፤
5. ሌሎች ከብድር ዋስትና ፈንዱ ጋር የተያያዙ ስራወችን ያከናውናል፡፡

1. Administration Board of Credit guarantee fund, hereinafter called the "board";
2. Micro and Small Enterprises Development Agency.

## 7. Board members of the credit Guarantee Fund

Board members of the credit guarantee fund are mainly concerned bodies from the point of view of micro and small enterprises development and credit guarantee fund administration, numbered from five up to seven and shall be nominated by the Head of Government.

## 8. Duty and Responsibility of the Board

The board shall, pursuant to this proclamation, have the following duties and responsibilities:

1. Hear reports concerning the credit guarantee fund;
2. Investigate and and thereby render decision if disagreement occurrs between credit organizations and micro and small enterprises development agency;
3. Strengthen the guarantee fund through searching for credit guarantee sources;
4. Issue its own directive concerning the board's meeting time and place, as well as internal working system;
5. Conduct other tasks that are related to credit guarantee fund.

## 9. ስለ ኤጀንሲዉ ሥልጣንና ተግባር

1. የፈንዱ አስተዳደር የእለት ከእለት ተግባራት በክልሉ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ይከናወናሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ሥር የሠፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ኤጀንሲው የፈንዱን አስተዳደር በተመለከተ የሚከተሉት ልዩ ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ. የፈንዱን አጠቃቀም በሚመለከት ወቅታዊ ሪፖርቶች ለቦርዱ ያቀርባል፣

ለ.የጥቃቅን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስ አቅርቦት እንዲሻሻልና ውጤታማ እንዲሆን በማጥናት ለቦርዱ ያቀርባል፣

ሐ.ቦርዱ የሚወስናቸውን ውሳኔዎች ያስፈጽማል፣

መ.ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በሚያቀርቡት ማመልከቻ መሰረት ብድር ማግኘት የሚያስችሉ መስፈርቶችን ያሟሉ መሆኑን በማጣራት ብድር ማግኘት እንደሚችሉ የሚገልጽ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣

ሠ.የዋስትና ፈንዱን በሚመለከት ከሚመለከታቸው ጋር ግንኙነት ያደርጋል፣

ረ. ከአበዳሪዎች ጋር ስምምነት ያደርጋል፣

ሰ. አበደሪዎች የሚያቀርቡትን የዋስትና ክፍያ ጥያቄ እየመረመረ በቦርዱ በጸደቀው መመሪያና አሰራር መሰረት ክፍያ ይፈጽማል፣

ሸ.አበዳሪዎች ብድር ለማስመለስ የሚያደርጉትን ጥረት ያግዛል፣

## 9. powers and Duties of the Agency

1. The day-to-day activities of the administration of the fund shall be conducted by the micro and small enterprises development agency of the region.
2. without prejudice to the general provision stated under sub article(1) of this Article, the agency shall have the following special powers and duties concerning to the fund administration:

a. submit periodic reports to the board concerning the utilization of the Fund;

b. conduct research for the improvement and effectiveness of the financial delivery of the micro and small enterprises and thereby submit same to the board;

c. Cause the board’s decisions be implemented;

d. Provide certificate of competence for getting loan by investigating whether they full fil the criteria set to get same based on the application lodged by the micro and small enterprises ;

e. Conduct relation with pertinent bodies concerning to the guarantee fund;

f. Enter in to agreement with creditors;

g. Execute payments pursuant to directive and procedure approved by the board by examining guarantee payment request submitted by the creditors thereon;

h. Support the effort that creditors exert to return back the credit;

ቀ. ብድር ለማግኘት የሚያስፈልጉ ሰነዶችን በማዘጋጀት ተበዳሪዎችን ያማክራል፣ ያግዛል፣

በ. የቦርዱ ሴክሬቴሪያት ሆኖ ያገለግላል፡፡

## ክፍል ሶስት
## ስለ ፈንዱ ተጠቃሚዎች እና ስለ አበዳሪ ተቋማት

### 10. የፈንዱ ተጠቃሚዎች

1. በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጅ ላይ በተቀመጡት የሥራ ዘርፎች ላይ ለመሰማራት ለሚፈልጉ ወይም ለተሰማሩ ለማምረትና አገልግሎት ለመስጠት ህጋዊ ፈቃድ ያላቸው በራሳቸዉና በቤተሰቦቻቸዉ ዋስትና ማቅረብ የማይችሉ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የፈንዱ ተጠቃሚዎች ይሆናሉ፡
2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 መሰረት በብድር ዋስትናው ፈንድ ተጠቃሚ ለመሆን ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከሚፈልጉት ጠቅላላ የብድር መጠን ከ15-30 በመቶ የሚሆነውን በቅድመ ብድር ቁጠባ መልኩ በአበዳሪ ተቋሙ መቆጠብ ይኖርባቸዋል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 2 የተጠቀሰዉን የቅድመ ብድር ቁጠባ ማሟላት የማይችሉ የትምህርት ተቋማት ወጣት ምሩቃን ይዘውት በሚወጡት አዋጭ የፕሮጀክት ሀሳቦችና ቴክኖሎጆዎች በመንግስት እና በአበዳሪ ተቋሙ 100% በብድር ዋስትና ብድር እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

i. Consult and support the debtors by preparing documents essencial to get credit;

j. Serve as the secretariat of the board.

## PART THREE
## Beneficiaries of the Fund and Credit Institutions

### 10. Fund Beneficiaries

1. Micro and Small Enterprises, which want to engage or are already engaged in the activity sector stipulated under the strategy of micro and small enterprises development, having legal permit to produce or deliver service, and can not produce guarantee by themselves as well as their families, shall be beneficiaries of the fund.
2. Micro and Small Enterprises shall, to be a beneficiary pursuant to sub article 1 of thia article, deposit 15-30 % of the loan in the credit institution in the form of pre-loan saving.
3. Young graduats of education institutions who are unable to fulfill the pre-loan saving stated under sub article 2 of this article shall be given 100% loan by the government and credit institutions credit guarantee based on their feasibility project and technologies.

## 11. የአበዳሪ ተቋማት መመልመያ መስፈርቶች

1. የአበዳሪ ተቋማት በዚህ አዋጅ መሰረት አበዳሪ መሆን የሚችሉት፣
   ሀ. የአገልግሎት አሰጣጣቸው ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ያለው ተደራሽነት፤
   ለ. የገንዘብና የአሰራር አቅማቸው ታይቶ ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የመመልመያ መስፈርቶችን ያሟላ አበዳሪ ተቋም በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ውል መያዝ አለበት፡፡

## 12. የአበዳሪ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

ከዚህ በላይ በአንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ /2/ መሰረት በኤጀንሲው የተመዘገቡና ውል የያዙ አበዳሪ ተቋማት የሚከተሉት ተግባራትና ሃላፊነቶች ይኖራቸዋል፡-

1. የተበዳሪዎችን የንግድ እቅድ መገምገምና ያቀረቡትን ፕሮጀክት አዋጭነቱን ማረጋገጥ፤
2. የተበዳሪዎችን ብድር አጠቃቀምና የንግድ እቅድ መከታተል፤
3. በስምምነቱ በሚገለጸው የጊዜ ገደብ መሰረት ለዋስትና ሠጭው አካል ሪፖርት ማቅረብ፤
4. የሚጠየቀው የዋስትና ክፍያ ጥያቄ ወቅቱን የጠበቀና በስምምነቱ መሰረት መሆኑን ማረጋገጥ፤
5. ከብድር ዋስትና ፈንዱ የዋስትና ክፍያ ጥያቄ ከመቅረቡ በፊት በሚቻለው መንገድ ሁሉ ተበዳሪ ብድሩን እንዲመልስ ጥረት ማድረግ፤

## 11. Selecting Criteria for Credit Institutions

1. Credit institutions may be creditor pursuant to this proclamation based on their:
   a. accessibility of service delivery to micro and small enterprises;
   b. financial and working system capacity.
2. A credit institution that fulfills the selscting criteria as per sub article 1 of this article shall enter in to contract with the micro and small enterprises development agency.

## 12. Duties and Responsibilities of Credit Institutions

Credit institutions , registered by and entered into contract with the agency pursuant to sub article 2 of article 11 hereof, shall have the following duties and responsibilities:

1. Evaluate the debtors business plan and ensure the feasibility of the submitted project;
2. Follow up the debtors loan utilization and business plan;
3. Submit a report to the body guarantee giving pursuant to the specified time limit in the agreement;
4. Ensure the request of guarantee payment to be periodic and pursuant to the agreement thereon;
5. Exert effort, as much as possible, for the returning back of the loan by the debtor before payment request be submitted from the credit guarantee fund;

6. ከብድር ጋር በተያያዘ ዋስትና ሰጭው አካል በየጊዜው የሚሰጣቸውን መመሪያዎች መከተልና መፈጸም፡፡

## ክፍል አራት

## ስለ ብድር ዋስትና ክፍያ አከፋፈል

### 13. በፈንዱ ስለሚከፈል የዋስትና ክፍያ መጠን

1. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጥ ብድር ኢንተርፕራይዞች አሁን ያላቸውን የመነሻ ወይም የስራ ማስኬጃ ወይም የመሳሪያ ችግር በማስወገድ ሰርተው ማትረፍ የሚያስችላቸውና ለአበዳሪው አካል መመለስ ያለበት ገንዘብ ነው፡፡
2. የአበዳሪው ገንዘብ ሳይመለስ የቀረ እንደሆነ ኪሳራውን መንግስትና አበዳሪ ተቋሙ የሚጋሩበት ስልት ይዘረጋል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የሰፈሩትን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ፡

ሀ. የሚበደሩትን የብድር መጠን ከ15%-30% በቅድመ ብድር ቁጠባ በአበዳሪ ተቋሙ ቆጥበው ቀሪውን ከ70%-85% የብድር መጠን ከአበዳሪ ተቋሙ ብድር/ማሽን ሊዝ የሚሰጣቸው የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የወሰዱት ገንዘብ ሳይመለስ ቢቀር ላልተመለሰው ገንዘብ እስከ ወለዱ 70 በመቶ በብድር ዋስትና ፈንዱ ይሸፈናል፡፡

6. Follow up and execute directives that the guarantee giving body shall give periodically in relation ti credit.

## Part Four

## Mode of Credit Guarantee Payment

### 13. Amount of Credit Payment paid by the Fund

1. The loan granted to micro and small enterprises shall be a money which enable them make profit by avoiding their problems of initial or working capital or machines; and be returned back to the credit entity.
2. There shall be established a system of sharing the loss by the government and credit institution, if the creditor's money may not be returned back.
3. Based on the provisions of sub article /1/ and /2 /of this article:

a. 70% of the unreturned money, including interest, shall be covered by the credit guarantee fund if micro and small enterprises which have deposited 15-30% of the loan given 70-85% loan/ machine lease by by the credit institute failed to return back the loan thereof;

ለ. ያለምንም ቅድመ ብድር ቁጠባ በአዋጭ ቢዝነስ ፕላን በአበዳሪ ተቋሙ 100% ብድር/ማሽን ሊዝ የሚሰጣቸው የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የወሰዱት ገንዘብ ሳይመለስ ቢቀር ላልተመለሰው ገንዘብ እስከ ወለዱ 97 በመቶ በብድር ዋስትና ፈንዱ ይሸፈናል፡፡

ሐ. በፊደል ሀ መሰረት ብድር/ማሽን ሊዝ ተሰጥቶ ሳይመለስ ለቀረ ገንዘብ እስከ ወለዱ 10 በመቶ በአበዳሪ ተቋሙ ኪሳራ የሚሸፈን ይሆናል፡፡

መ. በፊደል ለ መሰረት ብድር/ማሽን ሊዝ ተሰጥቶ ሳይመለስ ለቀረ ገንዘብ እስከ ወለዱ 3 በመቶ በአበዳሪ ተቋሙ ኪሳራ የሚሸፈን ይሆናል፡፡

## 14. የአበዳሪ ተቋማት የዋስትና ክፍያ ጥያቄ

1. አበዳሪ ተቋሙ ተበዳሪው በሚከተሉት ምክንያቶች ብድር መመለስ የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ ከዋስትና ፈንዱ ክፍያ መጠየቅ ይችላል፤

ሀ. በተፈጥሮ አደጋ የሀብት ውድመት ሲያጋጥም፣

ለ. ተበዳሪው በሞት ከመለየቱ ወይም ከባድ የአካል ጉዳት የደረሰበት ከመሆኑ የተነሣ ያለው ፕሮጀክት ወይም ድርጅት እዳውን የማይሸፍን ሲሆን፤

ሐ. በማናቸውም ሌላ ሁኔታ ተበዳሪ ኢንተርፕራይዞች ኪሳራ ሲያጋጥማቸውና ብድራቸውን ለመመለስ የማይችሉ ሲሆን፤

b. 97% of the unreturned money, including interest, shall be covered by the credit guarantee fund if micro and small enterprise which have been given 100% loan/ machine lease with out pre- credit saving , based on feasible business plan failed to return back the loan thereon;

c. 10% of the unreturned money, including interest, shall be covered by the credit institute if the loan/ machine lease given pursuant to letter /a/ hereof failed to be returned back.

d. 3% of the unreturned money, including interest, shall be covered by the credit institute if the loan/ machine lease given pursuant to letter /b/ failed to be returned back.

## 14. Guarantee Payment Request of Credit Institutions

1. The Credit institution may, if the debtor is proved not to return back the credit with the following reasons, request payment from the guarantee fund:

a. Damage of property occurs with natural disaster;

b. If the existing project or institution does not cover the liability due to the death of the debtor or serious bodily injury sustained against the same;

c. If the debtor institutions become bankrupt in any other reason and thereby unable to return back their loan.

2. የተበዳሪዎች ያልተመለሰ ብድር እስከ ወለዱ በብድር ዋስትና ፈንድ ቢሸፈንም ተበዳሪዎች ሀብት በሚያፈሩበት ጊዜ የመክፈል ግዴታ አለባቸዉ፡፡ አበዳሪ ተቋማትም ያልተመለሰውን ውዝፍ ብድር የመሰብሰብና የመንግስትን ድርሻ ወደ ብድር ዋስትና ፈንድ ሂሳብ የማስገባት ግዴታ አለባቸው፡፡

2. Though the unreturned loan, including interest, of the debtors shall be coverd by the credit guarantee fund, debtors are duty bound to pay same while they get wealth. Credit institutions shall also have a duty to collect the unreturned arrears loan and thereby transfer government's share in the credit guarantee fund account.

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## Part Five
## Miscellaneous Provisions

### 15. ተፈፃሚነት የማይኖራቸዉ ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ደንብና መመሪያ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረዉም።

### 15. Inapplicable Laws

Any proclamations, regulations and directives contrary to this proclamation shall not be applicable on matters provided in this proclamation.

### 16. ደንብ ወይም መመሪያ ስለማውጣት

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

### 16. Issuing regulation or directive

The Council of the Regional Government may issue regulations or directives necessary for the implementation of this proclamation.

### 17. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን □ምሮ የጸና ይሆናል፡፡

### 17. Effective Date

This proclamation shall come in to force as of its publication in the Zikre- Hig Gazzette of the Regional State.

ባህር ዳር
ሰኔ 20 ቀን 2004 ዓ.ም
አያሌው ጎበዜ
የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፕሬዚደንት

Done at Bahir Dar,
This 27th day of June, 2012.
Ayalew Gobezie
President of Amhara National Regional State